# የዓለምአቀፍ ማኅበረ እንባጠባቂዎች የልምምድ መስፈርትዎች

## መቅደም

የዓለምአቀፍ ፡ ማኅበረ ፡ እንባጠባቂዎች ፡ የልምምድ ፡ መስፈርትዎች ፡ ሥርና ፡ መሰረት ፡ የዓለምአቀፍ ፡ ማኅበረ ፡ እንባጠባቂዎች ፡ የግብረገብ ፡ ሰነድ ፡ ነው ።

የአንድአንድ ፡ የእንባጠባቂ ፡ መስሪያ ፡ ቤት ፡ የራሱ ፡ ድርጅታዊ ፡ ደንብ ፡ ወይም ፡ የመመሪያ ፡ ቃላት ፡ ያስፈልጋል ። ይኸም ፡ የአስተዳደር ፡ አለቅዎች ፡ ድጋፍ ፡ ያስፈልጋልና ፡ በዛ ፡ ድርጅት ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የእንባጠባቂ ፡ ጥቅምና ፡ የዚህ ፡ ጥቅም ፡ ግንኙነት ፡ ከዓለምአቀፍ ፡ ማኅበረ ፡ እንባጠባቂዎች ፡ ልምምድ ፡ መስፈርትዎች ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

## የልምምድ ፡ መስፈርትዎች

### ግዕዝነት (ነጻነት)

**፩፡፩** የእንባጠባቂ ፡ መስሪያ ፡ ቤትና ፡ እንባጠባቂው ፡ ግዕዝነት ፡ አላቸው ፡ ከሌላ ፡ ድርጅታዊ ፡ አካላት ።

**፩፡፪** እንባጠባቂው ፡ ከግዕዝነቱ ፡ ጋር ፡ ግጭትን ፡ የሚፈጥር ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ መያዝ ፡ የለበትም ።

**፩፡፫** ስለ ፡ ፩ ፡ ግለሰብእ ፡ ቅሬታ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ቅሬታ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ጸብና ፡ ጥል ፡ ዝንባሌዎች ፡ እንዴት ፡ መሳተፍና ፡ በምን ፡ አይነት ፡ መልክ ፡ መሳተፍ ፡ እንዳለበት ፡ እንባጠባቂው ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚወስነው ። እንባጠባቂው ፡ ቀጥታም ፡ በተመለከተም ፡ ጉዳይዎች ፡ መሳተፍ ፡ ይችላል ።

**፩፡፬** ሕግ ፡ የሚፈቅድ ፡ ያህል ፡ እንባጠባቂው ፡ ለየድርጅቱን ፡ መረጃዊ ፡ እውቀት ፡ ሁሉና ፡ ግለሰብእ ፡ ሁሉ ፡ ተዳርሶ ፡ አለው ።

**፩፡፭** ከሥሩ ፡ የሚገኙ ፡ ሠራተኞዎች ፡ ለመምረጥና ፡ የእንባጠባቂ ፡ መስሪያ ፡ ቤት ፡ ወጪና ፡ ገቢና ፡ ሥነሥርዓት ፡ ለማስተዳደር ፡ እንባጠባቂው ፡ ስልጣን ፡ አለው ።

### አለማዳላት

**፪፡፩** እንባጠባቂው ፡ የማያዳላ ፡ ገለልተኛም ፡ ወገን ፡ የለሽምና ፡ ቡድን ፡ አልባም ፡ መሆን ፡ አለበት ።

**፪፡፪** ሰዎችን ፡ በማገልግልና ፡ ቅሬታዎች ፡ በማሰላሰል ፡ እንባጠባቂው ፡ የማያዳላ ፡ ፍትሐዊና ፡ ሐቀኛ ፡ ለመሆን ፡ ይገሠግሣል ። ፍትሕና ፡ እኩልነት ፡ የሚያስፋፋ ፡ ሥነሥርዓት ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ እንባጠባቂው ፡ ድጋፍውን ፡ ይሰጣል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በድርጅቱ ፡ ውስጥ ፡ ድጋፍን ፡ ለማንኛውም ፡ ግለሰብእ ፡ አይሰጥም ።

**፪፡፫** እንባጠባቂው ፡ የማያዳላ ፡ ሆኖ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ በድርጅቱ ፡ ውስጥ ፡ ታላቅ ፡ ከሚባሉት ፡ መሪዎች ፡ ታላቅ ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ ከተራ ፡ ሠራተኛ ፡ መዋቅራት ፡ ግዕዝ ፡ መሆን ፡ አለበት ። እንባጠባቂው ፡ ከድርጅቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ የሕግ ፡ እሺታ ፡ ክፍል ፡ ሥር ፡ መሆን ፡ የለበትምና ፡ መዋቅራዊ ፡ ግንኙነትም ፡ ባይኑሮ ፡ ይሻላል ።

**፪፡፬** እንባጠባቂው ፡ ከአለማዳላቱ ፡ ጋር ፡ ግጭትን ፡ የሚፈጥር ፡ ተጨማሪ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ የለበትም ።

**፪፡፭** እንባጠባቂው ፡ ማንኛውም ፡ ጉዳይ ፡ ሲያሰላሰል ፡ ያ ፡ ጉዳይ ፡ የሚያካትት ፡ ግለሰብእ ፡ ሁሉ ፡ ተገቢ ፡ የሆኑ ፡ ቅሬታዎቻቸውንና ፡ ፍላጎትዎቻቸውን ፡ የማሰላሰል ፡ አላፊነት ፡ አለው ።

**፪፡፯** ችግርዎችን ፡ ይፈቱ ፡ ዘንድና ፡ ወደ ፡ ተገቢ ፡ መፍትሄ ፡ እንዲደርሱ ፡ እንባጠባቂው ፡ ሰዎችን ፡ ይረዳል ። ትእዛዝ ፡ ሳይሰጣቸው ፡ በጠቃሚ ፡ ጢያቄና ፡ አብሮ ፡ በማሰብ ፡ በንግግር ፡ ይመራቿል ።

## የምሥጢር ጥብቃ

**፫፡፩** እንባጠባቂው ፡ እርዳታ ፡ ከሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ የሚያደርገው ፡ ንግግርዎች ፡ እንደ ፡ ችሎታው ፡ መጠን ፡ በምሥጢር ፡ ይጠብቃል ። ይኸም ፡ ማለት ፡ እንባጠባቂው ፡ የእንግዳውን (እርዳታ የሚፈልግ ሰው) ፡ ማንነት ፡ ለሌላ ፡ አያሳውቅምና ፡ የማሳወቅም ፡ ግዴታ ፡ ሊኑሮ ፡ አይገባውም ። እንዲሁም ፡ ከእንግዳው ፡ የሚሰማው ፡ መረጃዊ ፡ እውቀት (information) ፡ በተለይ ፡ ማንነታቸውን ፡ ሊያሳውቅ ፡ የሚችል ፡ መረጃዊ ፡ እውቀት ፡ ለሌላ ፡ መግለጽ ፡ የለበትም ፡ ያለ ፡ እንግዳው ፡ ፈቃድ ። ይኸም ፡ ፈቃድ ፡ ከኢመደበኛ ፡ ንግግራቸው ፡ የሚመጣ ፡ ነው ። ይኸንን ፡ ይምሥጢር ፡ ጥብቃ ፡ ለመጣስ ፡ የሚፈቀደው ፡ እንባጠባቂው ፡ ከባድና ፡ ምራቅ ፡ የሚያስውጥ ፡ ጉዳት ፡ ለ፩ ፡ ስው ፡ መድረሱ ፡ የማይቀር ፡ ከመሰለው ፡ ነው ። እንባጠባቂው ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የእንባጠባቂ ፡ መስሪያ ፡ ቤት ፡ ጉዳይዎች ፡ አደገኝነት ፡ መጠን ፡ የሚወስነው ።

**፫፡፪** በጊዜ ፡ እንባጠባቂነት ፡ የሚያካሄድውት ፡ ንግግርዎች ፡ ከእንባጠባቂውና ፡ ከሌልዎች ፡ ጋር ፡ ምሥጢራዊ ፡ ናቸው ። ብቸኛው ፡ የምሥጢሩ ፡ ጠባቂም ፡ እንባጠባቂውና ፡ የመስሪያ ፡ ቤቱ ፡ ናቸው ። ሌልዎች ፡ ይኸ ፡ የምሥጢር ፡ መያዝ ፡ መብት ፡ ማስቀር ፡ አይችልውም ።

**፫፡፫** በድርጅቱ ፡ ውስጥ ፡ እንባጠባቂው ፡ መደበኛ ፡ ምስክርነት ፡ አይሰጥምና ፡ ከድርጅቱ ፡ ውጭ ፡ ምስክርነት ፡ መስጠትን ፡ ይቃወማል ። በተለይ ፡ ስለ ፡ እንግድዎቹ ፡ ጋር ፡ መገናኘቱና ፡ ስለ ፡ ሚያካፈሉት ፡ ምሥጢራዊ ፡ መረጃዊ ፡ እውቀት ። ፈቃዳቸውን ፡ ቢያገኝም ፡ እንኳን ፡ ሁኔታው ፡ አይለወጥም ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ እንባጠባቂ ፡ ሙያና ፡ ስለ ፡ እንባጠባቂው ፡ የመስሪያ ፡ ቤት ፡ እንደልቡ ፡ መናገር ፡ ይችላል ።

**፫፡፬** እንባጠባቂው ፡ ፩ ፡ ጉዳይን ፡ ከሥር ፡ ጀምረው ፡ እስከ ፡ መላ ፡ ድርጅቱ (systemically) ፡ ለማረም፡ ከሞከረ (ለምሳሌ ፡ ለመሪዎች ፡ የጸብና ፡ ጥል ፡ ጉዳይዎች ፡ ዝንባሌዎች ፡ ሕግጋትና ፡ ልምምድዎችን ፡ ማካፈል) ፡ እንባጠባቂው ፡ በተቻለው ፡ መጠን ፡ የግለሰብእ ፡ ማንነት ፡ መግለጽ ፡ የለበትም።

**፫፡፭** እንባጠባቂው ፡ ለድርጅቱ ፡ የሚያካፍል ፡ የሰውን ፡ ማንነት ፡ የሚገልጽ ፡ መዛግብት ፡ የለውም ።

**፫፡፮** እንባጠባቂው ፡ መረጃዊ ፡ እውቀትን (ለምሳሌ የጽሑፍ ማስታወሻዎች የስልክ መልእክትዎችና የቀን መቍጠሪያ ቀጠርዎች) ፡ ሰው (አስተዳደሪዎችም ቢሆኑም) ፡ ሊመርምረው ፡ የማይችልበት ፡ በተጠበቀ ፡ ቦታ ፡ ይይዛልና ፡ ለዚህ ፡ መረጃዊ ፡ እውቀት ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ የሚተገብረው ፡ የመደምሰስ ፡ ሥነሥርዓት ፡ አለው ።

**፫፡፯** ምሥጢርን ፡ እየጠበቀ ፡ እንባጠባቂው ፡ መረጃዊ ፡ እውቀትንና ፡ ዘገባን ፡ ያዘጋጃል ።

**፫፡፰** ከእንባጠባቂው ፡ ጋር ፡ የሚደረግ ፡ ንግግር ፡ እንደ ፡ በሕግ ፡ ደረጃ ፡ ማስጠንቀቂያ (notice) ፡ አይቆጠርም ። እንባጠባቂው ፡ ለድርጅቱ ፡ የሕግ ፡ ደረጃ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ አይቀበልምና ፡ አገልጋይም ፡ አይደለም ። የሕግ ፡ ደረጃ ፡

ማስጠንቀቂያ ፡ የሚቀበል ፡ ሥራ ፡ መያዝ ፡ አይችልም ። ነገር ፡ ግን ፡ እንባጠባቂው ፡ ግለሰብእን ፡ ወደ ፡ መደበኛ ፡ የሕግ ፡ ደረጃ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ተቀባይ ፡ ማስተላለፍ ፡ ይችላል ።

## ኢመደበኝነትና (ፊታ ያለ ዘዴና መላ) ሌላ መስፈርትዎች

**፬፡፩** የእንባጠባቂው ፡ አሠራር ፡ ኢመደበኛ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ መስማት ፡ መረጃዊ ፡ እውቀትን ፡ ማቅረብና ፡ መቀበል ፡ ጉዳይዎችን ፡ መለየትና ፡ ማመዛዘን ፡ ብዙ ፡ መፍትሄዎችን ፡ ማሰላሰልና - ፈቃደ ፡ እንግዳው ፡ ከእንባጠባቂው ፡ ውሳኔ ፡ ጋር ፡ ተስማምተው - ከ፫ኛም ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ኢመደበኛ ፡ ማማለድንና ፡ ማስታረቅን ፡ ይመስላል ። ሲቻል ፡ እንበጠባቂው ፡ የእንግዳውን ፡ እጅ ፡ ይዞ ፡ ከመምራት ፡ ይልቅ ፡ ያሰለጥኗል ።

**፬፡፪** እንባጠባቂው ፡ ኢመደበኛና ፡ አሠራሩ ፡ ከተመዘገቡ ፡ የረዳት ፡ ምንጬዎች (resources) ፡ ውጬ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ ጸብንና ፡ ጥልን ፡ ለመፍትሃት ፡ ሙከራ ፡ ያደርጋልና ፡ ተገቢ ፡ ሲሆን ፡ ድርጅትአቀፍ ፡ ሥነሥርዓታዊና ፡ ደንባዊ ፡ ችግርዎችን ፡ ይመለክታል ።

**፬፡፫** እንባጠባቂው ፡ ለድርጅቱ ፡ ሠራተኛን ፡ የሚአስር ፡ ድምዳሜ ፡ መደምደም ፡ ውሳኔም ፡ መወሰን ፡ ሕግንም ፡ ማወጅና ፡ መደበኛ ፡ ፍርድንም ፡ መፍረድ ፡ አይችልም ።

**፬፡፬** እንበጠባቂው ፡ መደበኛ ፡ የሆኑ ፡ የረዳት ፡ ምንጬዎችን ፡ ተባባሪ ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ ተኪ ፡ አይሆንም ። የእንባጠባቂ ፡ መስሪያ ፡ ቤት ፡ ለመጠቀም ፡ የጠቃሚዎቹን ፡ ሁሉ ፡ ፈቃድ ፡ ይጠይቃልና ፡ በማንኛውም ፡ ድርጅታዊ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ መደበኛ ፡ የቅሬታ ፡ ማቅረብ ፡ ሥነሥርዓት ፡ ውስጥ ፡ የግዳጅ ፡ ደረጃ ፡ ሆኖ ፡ ሊገኝ ፡ አይችልም ።

**፬፡፭** እንባጠባቂው ፡ በመደበኛ ፡ ምርመራና ፡ ዳኝነት ፡ ሥነሥርዓት ፡ ሱታፌ ፡ የለውም ። መደበኛ ፡ ምርመራ ፡ የሌላ ፡ ሰዎች ፡ ሥራ ፡ ይሁን ። ግለሰብእ ፡ እንባጠባቂውን ፡ ስለ ፡ መደበኛ ፡ ምርመራ ፡ ከጠየቀው ፡ እንባጠባቂው ፡ ግለሰቡን ፡ ወደ ፡ ትክክለኛው ፡ የመስሪያ ፡ ቤትዎች ፡ ወይም ፡ ሠራተኛዎች ፡ ይልከዋል ።

**፬፡፮** እንባጠባቂው ፡ ስለ ፡ ሕግጋትና ፡ ሥነሥርዓት ፡ ያላቸው ፡ የመላ ፡ ድርጅቱን ፡ ዝንባሌዎች ፡ ሁኔታዎችና ፡ ቅሬታዎችን ፡ ይመለከታል ። ይኸም ፡ ማለት ፡ ይሰውን ፡ ማንነት ፡ ሳያጋልጥ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሊመጡ ፡ የሚችሉም ፡ ሁኔታዎችና ፡ ቅሬታዎችን ፡ የመለከታል ። በደንብ ፡ እንዲጠቀሱም ፡ ምክሩን ፡ ያቀርባል ።

**፬፡፯** እንባጠባቂው ፡ በዓለምአቀፍ ፡ ምኅበረ ፡ እንባጠባቂዎች ፡ ግብረገብና ፡ የልምምድ ፡ መስፈርትዎች ፡ ይመራል ። በእንበጠባቂ ፡ ሙያ ፡ ተከታታይ ፡ ትምህርትን ፡ መፈለግና ፡ ማግኘት ፡ ለራሱና ፡ ከሥሩ ፡ ለአሉት ፡ ሠራተኛዎች ፡ ይፈቅዳል ።

**፬፡፰** ሰዎች ፡ የእንባጠባቂ ፡ መስሪያ ፡ ቤትን ፡ ታማኝ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ስለ ፡ ሚያምኑ ፡ እንባጠባቂው ፡ ለዚህ ፡ እምነት ፡ ብቁ ፡ ሆኖ ፡ ይገኝ ፡ ዘንድ ፡ ይገሠግሣል ።